የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፭
አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፰ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20[th] Year No. 5
ADDIS ABABA 27[th] December, 2013


ማውጫ


ደንብ ቁጥር ፫፻፫/፪ሺ፮ ዓ.ም
የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ማቋቋሚያ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ..........ገጽ ፯ሺ፩፻፳፮


CONTENTS


Regulation No. 303 /2013
Ethiopian Electric Utility Establishment Council of Ministers Regulation ..........................Page 7126


## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፫/፪ሺ፮

## የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩) (ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፫/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. መቋቋም

፩/ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

### ፫. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

የውኃ፤ የመስኖ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

### ፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ሊኖረው ይችላል፡፡

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 303/2013

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN ELECTRIC UTILITY

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 47(1)(a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Electric Utility Establishment Council of Ministers Regulation No. 303/2013".

### 2. Establishment

1/ The Ethiopian Electric Utility (hereinafter the "Enterprise") is hereby established as a public enterprise.

2/ The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

### 3. Supervising Authority

The Ministry of Water, Irrigation and Energy shall be the supervising authority of the Enterprise.

### 4. Head Office

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.


ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit Gazette P.O.box 80,001

፭. ዓላማ

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ መስመሮችን የግንባታና የጥገና ሥራዎችን ማከናወን ፣ እንደአስፈላጊነቱ የማከፋፈያ መስመሮችን ግንባታ በሥራ ተቋራጭ ማሠራት፤

፪/ የኤሌክትሪክ ኃይል የማከፋፈያ መስመሮችን ማስተዳደር እና ጅምላ የኤሌክትሪክ ኃይል ገዝቶ ለደንበኞች የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ሽያጭ ሥራዎችን ማከናወን፤

፫/ የኤሌክትሪክ ታሪፍ ማሻሻያ ሀሳብ ማቅረብ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ፤

፬/ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚያወጣውን መመሪያና የፖሊሲ አቅጣጫ መሠረት በማድረግ ቦንድ መሸጥና በዋስትና ማስያዝ እና ከአገር ውስጥና ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል መደራደርና መፈራረም፤

፭/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማካሄድ፡፡

፮. ካፒታል

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፷፬ቢሊዮን ፯፻፲፭ሚሊዮን ፰፻፳፪ሺ ፮፻፺፫ብር ከ፳ ሣንቲም (ስልሳ አራት ቢሊዮን ሰባት መቶ አሥራ አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃያ ሁለት ሺ ስድስት መቶ ዘጠና ሦስት ብር ከሃያ ሣንቲም) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፲፮ቢሊዮን ፩፻፸፰ሚሊዮን ፱፻፶፭ሺ ፮፻፸፫ ብር ከ፴ሣንቲም ( አሥራ ስድስት ቢሊዮን አንድ መቶ ሰባ ስምንት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃምሳ አምስት ሺ ስድስት መቶ ሰባ ሦስት ብር ከሠላሳ ሣንቲም) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

፯. ኃላፊነት

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

፰. ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

፱. የተሻረ ደንብ

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፸/፪ሺ፪ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

5. Purpose

The purposes for which the Enterprise is established are:

1/ to construct and maintain electric distribution networks; to contract out the distribution networks construction to contractors as required;

2/ to administer electric distribution networks, to purchase bulk electric power and sell electric energy to customers;

3/ to initiate electric tariff amendments and, upon approval, to implement same;

4/ in line with directives and policy guidelines issued by the Ministry of Finance and Economic Development, to sell and pledge bonds and to negotiate and sign loan agreements with local and international financial sources;

5/ to undertake any other related activities necessary for the attainment of its purposes.

6. Capital

The authorized capital of the Enterprise is Birr 64,715,822,693.20 ( Sixty Four Billion Seven Hundred Fifteen Million Eight Hundred Twenty Two Thousand Six Hundred Ninety Three Birr and Twenty Cents) of which Birr 16,178,955,673.30 (Sixteen Billion One Hundred Seventy Eight Million Nine Hundred Fifty Five Thousand Six Hundred Seventy Three Birr and Thirty Cents) is paid up in cash and in kind.

7. Liability

The Enterprise may not be held liable beyond its total asset.

8. Duration

The Enterprise is established for an indefinite duration.

9. Repealed Regulation

The Ethiopian Electric Power Corporation Re-Establishment Council of Ministers Regulation No. 170/2009 is hereby repealed.

**፲. የመብትና ግዴታ መተላለፍ**

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፸/፪ሺ፩ እንደገና ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን መብቶችና ግዴታዎች ከኃይል ማመንጫ፣ ማስተላለፊያና ማከፋፈያ ጣቢያ ሥራዎቹ ጋር በቀጥታ የተያያዙትን መብቶችና ግዴታዎች ሳይጨምር በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፈዋል፡፡

**፲፩. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከህዳር ፴ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፰ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

**10. Transfer of Rights and Obligations**

The rights and obligations of the Ethiopian Electric Power Corporation re-established under the Council of Ministers Regulation No. 170/2009, other than those rights and obligations directly related to its power generation, transmission and substation activities, are hereby transferred to the Enterprise.

**11. Effective Date**

This Regulation shall come into force as of the 9th day of December, 2013.

Done at Addis Ababa, this 27th day of December, 2013.

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**